- ምክንያቱም መሬቱ በደንብ የታረሰ ስለሆነ ነው።

- በመልካሙ መሬት የተመሰሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ሙሉ በሙሉ ያመኑና ብዙ ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።

- እነዚህ ሰዎች በኃጢአት መወለዳቸውን ያውቃሉ።

- እነዚህ ሰዎች ኃጢአታቸው የዘላለም ሞት እንደሚገባው ያውቃሉ።

- እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ብቻ ሊያድናቸው እንደሚችል ያውቃሉ።

- እነዚህ ሰዎች በአዳኙ በኢየሱስ ያምናሉ።

- እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ያምናሉ፣ ብዙ ፍሬም ያፈራሉ።

- የእናንተስ ልባችሁ እንደ መልካሙ መሬት ነውን?



## ትምህርት 55

1. ፈሪሳውያን ኢየሱስን ይጠሉት የነበረው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እርሱ አዳኙ አምላክ መሆኑን ስለነገራቸው።

2. ፈሪሳውያን ኢየሱስን በሌላ በምን ይጠሉት ነበር?

ሀ- ኢየሱስ ኃጢአተኞች መሆናቸውንና ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ስለነገራቸው።

3. ፈሪሳውያን ኢየሱስን በሌላ በምን ይጠሉት ነበር?

ሀ- ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ይከተሉት ስለነበር በመቅናት።

4. ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አንዷን ቢያፈርስ፣ ፈሪሳውያን ምን ያደርጉ ነበር?

ሀ- ኢየሱስን በሞት ይቀጡት ነበር።

5. ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አንዷን እንኳን አፍርሷል?

ሀ- አላፈረሰም።

6. ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አንዷን እንኳን በፍጹም ያላፈረሰው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ ፍጹም ስለሆነ ነው።

ለ- ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ነው።

ሐ- ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት ስለሆነ ነው።

መ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን በሁሉም ነገር ስለታዘዘ ነው።

7. ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ያልታዘዘው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ፈርሳውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ስለለወጡ ነው።

8. ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዞች የለወጡት እንዴት ነበር?

ሀ- ፈሪሳውያን የለወጡት፥የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ውሸታም በማድረግ፥ በእግዚአብሔር ትእዛዞች ላይ የራሳቸውን ሕጎች በመጨመር ነው።

9. ኢየሱስ በፈሪሳውያን ላይ የተቆጣው ለምን ነበር?

ሀ- ኢየሱስ የተቆጣው፥ የልባቸውን ደንዳናነት አይቶ ነው።

10. ኢየሱስ ልባቸው ደንዳና መሆኑን እንዴት አወቀ?

ሀ- ኢየሱስ የሰውን ልብ ሁሉ መመልከት ይችላል።

ለ- ኢየሱስ የሰውን ልብ ሙሉ በሙሉ ያውቃል።

11. ኢየሱስ እጁ የሰለለችውን ሰው ከፈወሰ በኋላ ፈሪሳውያን ምን አደረጉ?

ሀ- ከምኩራብ ውጥተው ኢየሱስን እንዴት እንደሚገድሉት መማከር ጀመሩ።

12. ርኩሳን መናፍስት ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ብለው የጠሩት ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ርኩሳን መናፍስት፥ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ መምጣቱን ስላወቁ ነው።

13. ርኩሳን መናፍስት በኢየሱስ እንድታምኑ የማይፈልጉት ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ከእነርሱ ግዛት እንድታመልጡ ስለማይፈልጉ ነው።

14. እርሱን ከተከተሉት ሰዎች መካከል የእርሱ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ኢየሱስ የመረጣቸው ስንቱን ነበር?

ሀ- አሥራ ሁለቱን።

15. እነዚህ አሥራ ሁለት ሰዎች ማን ተብለው ይጠሩ ነበር?

ሀ- ሐዋርያት።



ገንዘብ ማግኘት ከእግዚአብሔር የበለጠ አስፈላጊ ነው።

- እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር እናምናለን ይላሉ ነገር ግን ትልቅ ቤት ወይም ብዙ ከብት ማግኘት ለእነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር የበለጠ አስፈላጊ ነው።

- የእናንተ ልብ ብዙ እሾክ እንዳለበት መሬት ነው?

- ኢየሱስ «የአንዳንድ ሰዎች ልብ እንደ መልካሙ መሬት ነው» አለ።

ማርቆስ 4፡20

20- ኢየሱስ እንዲህ አለ «ሌሎቹ በመልካም መሬት ላይ የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤ እዚህም ቃሉን ሰምተው የሚቀበሉና ሠላሳ፣ ሥልሳ፣ መቶም ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።»

- የመልካሙ መሬት ዐፈር እንዴት ያለ ነው?

- በደንብ የታረሰ መሬት ነው።

- አንድ ገበሬ በመልካም መሬት ላይ ዘሩን ቢዘራ፣ መሬቱ ፍሬ ይሰጠዋል?

- አዎን።

- ለምን?

- ምክንያቱም መሬቱ ጠንካራ ስላልሆነ ነው።

- ምክንያቱም አፈሩ ጥልቀት ስላለው ነው።

- ምክንያቱም መሬቱ እሾኽ ስለሌለው ነው።

19- ነገር ግን የዚህ ዓለም ውጣ ውረድ፣ የሀብት አጓጊነት እንዲሁም የሌሎች ነገሮች ምኞት ቃሉን አንቀው በመያዝ ፍሬ እንዳያፈራ ያደርጉታል።»

- ብዙ እሾሆች ያሉበት ዐፈር እንዴት ያለ ዐፈር ነው?
- ታርሶ የሚያውቅ ዐፈር ነው።

- አንድ ገበሬ ብዙ እሾህ ባለበት መሬት ላይ ዘር ቢዘራ፣ መሬቱ ፍሬ ይሰጠዋል?

- አይሰጠውም።

- ብዙ እሾህ ባለበት መሬት ላይ የተዘራው ዘር ፍሬ የማይሰጠው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ብዙዎቹ እሾኾች ተክሉን ስለሚያንቁት ነው።

- ኢየሱስ፣ «የብዙ ሰዎች ልብ እሾኽ እንደ ሞሉት መሬት ነው» አለ።

- እሾህ ባለበት መሬት የሚመስሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

- እነዚህ ሰዎች «በእግዚአብሔር እናምናለን» የሚሉ፥ ነገር ግን የፍላጎታቸው መሟላት ከእግዚአብሔር የበለጠ አስፈላጊያቸው የሆኑ ሰዎች ናቸው።

- እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር እናምናለን ይላሉ ነገር ግን ለእነርሱ ብዙ



- ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ከመረጠ በኋላ፣ ሕዝቡን ማስተማር ቀጠለ።

ማርቆስ 4፡1

1- በሌላ ጊዜ ደግሞ በባሕሩ አጠገብ ያስተምር ጀመር። እርሱ ባለበት አካባቢ እጅግ ብዙ ሕዝብ ስለ ተሰበሰበ፣ በባሕሩ ላይ ወዳለች ጀልባ ገብቶ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ በባሕሩ ዳርቻ ባለው ስፍራ ላይ ተሰብስቦ ነበር።

- ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ኢየሱስ በባሕሩ ውስጥ ባለች ጀልባ ላይ ተቀመጠ።

- ኢየሱስ ጀልባ ላይ ሆኖ በባሕሩ ዳርቻ ሆነው የሚሰሙትን ሰዎች አስተማረ።

ማርቆስ 4፡2ሀ

2- ኢየሱስ ብዙ ነገሮችን በምሳሌ አስተማራቸው።

- ኢየሱስ ሕዝቡን በምሳሌ አስተማራቸው።

- ምሳሌ ምንድን ነው?

- ምሳሌ የእግዚአብሔርን እውነት የሚያስተምር ታሪክ ነው።

- ኢየሱስ ሕዝቡን በምሳሌ ማስተማር የጀመረው ለምንድን ነው?

- ምንም እንኳን ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ቢከተሉትም በኢየሱስ ስላላመኑ።

- ምንም እንኳ ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ቢከተሉትም፣ ትምህርቱን አምነው አልተቀበሉም ነበር።

- ብዙ ሰዎች ኢየሱስን የተከተሉት ትምህርቱን አምነው ስለተቀበሉ ሳይሆን፣ ሰዎችን ሲፈውስ ለማየት ነበር።

- ብዙ ሰዎች ኢየሱስን የተከተሉት ትምህርቱን አምነው ስለተቀበሉ ሳይሆን፣ ርኩስ መናፍስትን ከሰዎች ሲያወጣ ለማየት ነበር።

- ብዙ ሰዎች ትምህርቱን አምነው ስላልተቀበሉ፥ ኢየሱስ ሰዎችን በምሳሌ ማስተማር ጀመረ።

- ኢየሱስ ሲያስተምር፣ በምሳሌ ያስተምራቸው ነበር።

- ኢየሱስ የዘሪውን ምሳሌ ነገራቸው።

ማርቆስ 4፡2ለ-12

2- እንዲህም አላቸው፤

3- «ስሙ፤ አንድ ዘሪ ዘር ሊዘራ ወጣ።

4- ዘሩን በሚዘራበትም ጊዜ አንዳንዱ መንገድ ላይ ወደቀ፤ ወፎችም መጥተው ለቅመው በሉት።

5- ሌላው በቂ ዐፈር በሌለበት በጭንጫ ቦታ ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ጥልቀት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤

6- ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፤ ሥር ስላልነበረውም ደረቀ፤

7- ሌላው ዘር ደግሞ በእሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም አድጎ የዘሩን ተክል ስላነቀው ፍሬ አላፈራም።



- በጭንጫ መሬት ላይ የተዘራው ዘር ፍሬ የማይሰጠው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ዐፈሩ ጥልቀት ስለሌለው ሥሮቹ ዐፈሩ ውስጥ ዘልቀው መግባት ስለማይችሉ ነው።

- ኢየሱስ «የአንዳንድ ሰዎች ልብ እንደ ጭንጫ መሬት ነው» አለ።

- በጭንጫ መሬት የተመሰሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

- እነዚህ ሰዎች ላይ ላዩን ብቻ «በእግዚአብሔር እናምናለን» የሚሉ፣ ውስጣቸው ሲታይ ግን እምነት የሌላቸው ናቸው።

- እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር እናምናለን ይላሉ ችግሮች ሲከሰቱ ግን፣ ከእግዚአብሔር እውነት ያፈነግጣሉ።

- እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር እናምናለን ይላሉ ነገር ግን ሰዎች ሲያስፈዙባቸው፣ ከእግዚአብሔር እውነት ያፈገፍጋሉ።

- እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር እናምናለን ይላሉ ነገር ግን መናፍስትን በመፍራት ከእግዚአብሔር እውነት ያፈገፍጋሉ።

- ልባችሁ እንደ ጭንጫ መሬት ነው?

- ኢየሱስ፣ የአንዳንድ ሰዎች ልብ እሾክ እንዳለበት መሬት ነው አለ።

ማርቆስ 4፡18-19

18- [ኢየሱስ እንዲህ አለ] «ሌሎቹ ደግሞ በእሾኽ መካከል የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን መስማት ይሰማሉ፤

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰሙበት ጊዜ፣ ወዲያውኑ ይረሱታል።

- ሰይጣን መጥቶ ቃሉን ይወስድባቸዋል።

- ልባችሁ እንደ መንገድ ነው?

- ኢየሱስ «የአንዳንድ ሰዎች ልብ እንደ ጭንጫ መሬት ነው» አለ።

ማርቆስ 4፡16-17

16- እንዲሁም ሌሎች በጭንጫ ቦታ ላይ የተዘራውን ዘር
ይመስላሉ፤ ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ በደስታ ይቀበሉታል፤

17- ነገር ግን ሥር የሌላቸው ስለ ሆኑ የሚቈዩት ለጥቂት ጊዜ ብቻ
ነው፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በመጣ ጊዜ ወዲያውኑ
ይሰናከላሉ።

- ጭንጫ ዐፈር እንዴት ያለ ዐፈር ነው?

- ጭንጫ ዐፈር ጥልቀት የሌለው ዐፈር ነው።

- ጥልቀት የሌለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ከሥሩ ዐለት ስላለ ነው።

- አንድ ገበሬ ዘሩን በጭንጫ መሬት ላይ ቢዘራ መሬቱ ፍሬ ይሰጠዋል?

- አይሰጠውም።



8- ሌላው ዘር ደግሞ በመልካም መሬት ላይ ስለ ወደቀ በቅሎ
አደገ፤ ፍሬም ሰጠ፤ አንዱ ሠላሳ፣ አንዱ ሥልሳ ሌላውም መቶ ፍሬ
አፈራ።

9- ቀጥሎም ኢየሱስ፣ «የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ» አለ።

10- ብቻውን በሆነ ጊዜ፣ ዐሥራ ሁለቱና አብረውት የነበሩት ሌሎች
ስለምሳሌዎቹ ጠየቁት፤

11- እርሱም፣ «ለእናንተ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር
ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት ግን ነገር ሁሉ በምሳሌ ይነገራቸዋል፤

12- ይኸውም፣ «ማየቱን እንዲያዩ እንዳያስተውሉትም፣ መስማቱን
እንዲሰሙ ልብ እንዳይሉትም፤ እንዳይመለሱና ኀጢአታቸው
እንዳይሰረይላቸው ነው» አላቸው።

- በኢየሱስ ያላመኑት ሰዎች ምሳሌዎችን አይገነዘቡም ነበር።

- በኢየሱስ ያመኑት ሰዎች ግን ምሳሌዎችን ተረድተው ስለ እግዚአብሔር ብዙ ይማሩ ነበር።

- እግዚአብሔር የሚያስተምራችሁ እውነትን ማወቅ ከፈለጋችሁ ብቻ ነው።

- እውነትን ማወቅ ካልፈለጋችሁ እግዚአብሔር አያስተምራችሁም።

- ደቀ መዛሙርት የምሳሌውን ትርጉም በጠየቁት ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡

ማርቆስ 4፡13-14

13- ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ «ይህን ምሳሌ

አልተረዳችሁትምን?  ታዲያ ሌሎቹን ምሳሌዎች ሁሉ እንዴት ልትረዱ ትችላላችሁ?

14- ዘሪው ቃሉን ይዘራል።»

- በምሳሌው ውስጥ ዘሩ ምንድን ነው?

- ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው።
- በምሳሌው ውስጥ ዘሪው ማን ነው?

- ዘሪው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምረው ነው።

- ኢየሱስ «ዘር የሚዘራባቸው ልዩ ልዩ መሬቶች እንዳሉ ሁሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል የሚዘራባቸው ልዩ ልዩ ልብ አለ» አለ።

- ኢየሱስ «የአንዳንድ ሰዎች ልብ እንደ መንገድ ነው» አለ።

ማርቆስ 4፡15

15- አንዳንድ ሰዎች በመንገድ ላይ የወደቀውን ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ ሰይጣን ወዲያውኑ መጥቶ በውስጣቸው የተዘራውን ቃል ይወስደዋል።»

- የመንገድ ላይ ዐፈር እንዴት ያለ ዐፈር ነው?

- በጣም ጠንካራ ነው።

- በጣም ጠንካራ የሚሆነው ለምንድን ነው?



- ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ስለሚረግጡት ነው።

- ገበሬ በጠንካራ መንገድ ላይ ዘር ቢዘራ መሬቱ ፍሬ ይሰጠዋል?
- አይሰጠውም።

- በጠንካራ መንገድ ላይ የተዘራው ዘር ፍሬ የማይሰጠው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም መንገዱ ጠንካራ ስለሆነ ዘሩ ዐፈሩ ውስጥ መግባት ስለማይችል ነው።

- ከዚያም ወፎች ወይም ሌሎች እንስሳት መጥተው ዘሩን ስለሚለቅሙ ማደግ አይችልም።

- ኢየሱስ «የአንዳንድ ሰዎች ልብ እንደ ጠንካራ መንገድ ነው» አለ።

- በመንገድ የሚመሰሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

- ልባቸው ጠንካራ የሆኑ ሰዎች ናቸው።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል ወደ ልባቸው ዘልቆ መግባት አይችልም።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መስማት አይፈልጉም።

- እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲያስተምራቸው አይፈልጉም።
- እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን መከተል አይፈልጉም።

- እነዚህ ሰዎች የቅድመ አባቶቻቸውን መንገድ ብቻ መከተል ይፈልጋሉ።